# 2013 መጽሓፍ ቅዱስ ብሉይና ኣዲስ ኪዳን

PDF version for mobile devices and offline use. Not for print

The source of the bible is from bible.org. It is possible that the document contains spelling errors or some missing verses. Errors are corrected continuously and a new revised version is available for download at www.geezexperience.com/amharicbible/

Please do write us email if you find any typing error at info@geezexperience.com or visit www.geezexperience.com/amharicbible/ to submit your correction.

©copyright pdf format geezexperience.com. content bible.org

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉትን፥ ሚዛኑ እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሆነውን አንድ የብር ወጭት፥ ሚዛኑም ሰባ ሰቅል የሆንውንአንድ የብር ድስት፤ 20 ዕጣንም የተሞላውን ሚዛኑ አሥር ሰቅል የሆነውን አንድ የወርቅ ጭልፋ፤ 21 ለሚቃጠልም መሥዋዕት አንድ ወይፈን፥ አንድ አውራ በግ፥ አንድ የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት፤ 22 ለኃጢአትም መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል፤ 23 ለደኅነትም መሥዋዕት ሁለት በሬዎች፥ አምስት አውራ በጎች፥ አምስት አውራ ፍየሎች፥ አምስት የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች አቀረበ የሶገር ልጅ የናትናኤል መባ ይህ ነበረ።

24 በሦስተኛውም ቀን የዛብሎን ልጆች አለቃ የኬሎን ልጅ ኤልያብ፤ 25 መባውም ለእህል ቍርባን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ፥ ሚዛኑ እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ወጭት፥ ሚዛኑም ሰባ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ድስት፤ 26 ዕጣንም የተሞላ ሚዛኑ አሥር ሰቅል የሆነ አንድ የወርቅ ጭልፋ፤ 27 ለሚቃጠልም መሥዋዕት አንድ ወይፈን፥ አንድ አውራ በግ፥ አንድ የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት፤ 28 ለኃጢአትም መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል፤ 29 ለደኅንነትም መሥዋዕት ሁለት በሬዎች፥ አምስት አውራ በጎች፥ አምስት አውራ ፍየሎች፥ አምስት የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች ነበረ፤ የኬሎን ልጅ የኤልያብ መባ ይህ ነበረ።

30 በአራተኛውም ቀን የሮቤል ልጆች አለቃ የሰዲዮር ልጅ ኤሊሱር፤ 31 መባውም ለእህል ቍርባን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ፥ ሚዛኑ እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ወጭት፥ ሚዛኑም ሰባ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ድስት፤ 32 ዕጣንም የተሞላ ሚዛኑ አሥር ሰቅል የሆነ አንድ የወርቅ ጭልፋ፤ 33 ለሚቃጠልም መሥዋዕት አንድ ወይፈን፥ አንድ አውራ በግ፥ አንድ የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት፤ 34 ለኃጢአትም መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል፤ 35 ለደኅንነትም መሥዋዕት ሁለት በሬዎች፥ አምስት አውራ በጎች፥ አምስት አውራ ፍየሎች፥ አምስት የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች ነበረ፤ የሰዲዮር ልጅ የኤሊሱር መባ ይህ ነበረ።

36 በአምስተኛውም ቀን የስምዖን ልጆች አለቃ የሱሪሰዳይ ልጅ ሰለሚኤል፤ 37 መባውም ለእህል ቍርባን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ፥ ሚዛኑ እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ወጭት፥ ሚዛኑም ሰባ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ድስት፤ 38 ዕጣንም የተሞላ ሚዛኑ አሥር ሰቅል የሆነ አንድ የወርቅ ጭልፋ፤ 39 ለሚቃጠልም መሥዋዕት አንድ ወይፈን፥ አንድ አውራ በግ፥ አንድ የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት፤ 40 ለኃጢአትም መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል፤ 41 ለደኅንነትም መሥዋዕት ሁለት በሬዎች፥ አምስት አውራ በጎች፥ አምስት አውራ ፍየሎች፥ አምስት የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች ነበረ፤ የሱሪሰዳይ ልጅ የሰለሚኤል መባ ይህ ነበረ።

42 በስድስተኛውም ቀን የጋድ ልጆች አለቃ የራጉኤል ልጅ ኤሊሳፍ፤ 43 መባውም ለእህል ቍርባን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ፥ ማዛኑ እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ወጭት፥ ሚዛኑም ሰባ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ድስት፤ 44 ዕጣንም የተሞላ ሚዛኑ አሥር ሰቅል የሆነ አንድ የወርቅ ጭልፋ፤ 45 ለሚቃጠልም መሥዋዕት አንድ ወይፈን፥ አንድ አውራ በግ፥ አንድ የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት፤ 46 ለኃጢአትም መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል፤ 47 ለደኅነትም መሥዋዕት ሁለት በሬዎች፥ አምስት አውራ በጎች፥ አምስት አውራ ፍየሎች፥ አምስት የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች ነበረ፤ የራጉኤል ልጅ የኤሊሳፍ መባ ይህ ነበረ።

48 በሰባተኛውም ቀን የኤፍሬም ልጆች አለቃ የዓሚሁድ ልጅ ኤሊሳማ፤ 49 መባውም ለእህል ቍርባን

በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ፥ ሚዛኑ እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ወጭት፥ ሚዛኑ ሰባ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ድስት፤ [50] ዕጣንም የተሞላ ሚዛኑ አሥር ሰቅል የሆነ አንድ የወርቅ ጭልፋ፤ [51] ለሚቃጠልም መሥዋዕት አንድ ወይፈን፥ አንድ አውራ በግ፥ አንድ የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት፤ [52] ለኃጢአትም መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል፤ [53] ለደኅንነትም መሥዋዕት ሁለት በሬዎች፥ አምስት አውራ በጎች፥ አምስት አውራ ፍየሎች፥ አምስት የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች ነበረ፤ የዓሚሁድ ልጅ የኤሊሳማ መባ ይህ ነበረ።

[54] በስምንተኛውም ቀን የምናሴ ልጆች አለቃ የፍዳሱር ልጅ ገማልኤል፤ [55] መባውም ለእህል ቍርባን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ፥ ሚዛኑ እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ወጭት፥ ሚዛኑም ሰባ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ድስት፤ [56] ዕጣንም የተሞላ ሚዛኑ አሥር ሰቅል የሆነ አንድ የወርቅ ጭልፋ፤ [57] ለሚቃጠል መሥዋዕት አንድ ወይፈን፥ አንድ አውራ በግ፥ አንድ የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት፤ [58] ለኃጢአትም መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል፤ [59] ለደኅንነትም መሥዋዕት ሁለት በሬዎች፥ አምስት አውራ በጎች፥ አምስት አውራ ፍየሎች፥ አምስት የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች ነበረ፤ የፍዳሱር ልጅ የገማልኤል መባ ነበረ።

[60] በዘጠነኛውም ቀን የብንያም ልጆች አለቃ የጋዴዮን ልጅ አቢዳን፤ [61] መባውም ለእህል ቍርባን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ፥ ሚዛኑ እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ወጭት፥ ሚዛኑም ሰባ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ድስት፤ [62] ዕጣንም የተሞላ ሚዛኑ አሥር ሰቅል የሆነ አንድ የወርቅ ጭልፋ፤ [63] ለሚቃጠልም መሥዋዕት አንድ ወይፈን፥ አንድ አውራ በግ፥ አንድ የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት፤ [64] ለኃጢአትም መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል፤ [65] ለደኅንነትም መሥዋዕት ሁለት በሬዎች፥ አምስት አውራ በጎች፥ አምስት አውራ ፍየሎች፥ አምስት የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች ነበረ፤ የጋዴዮን ልጅ የአቢዳን መባ ይህ ነበረ።

[66] በአሥረኛውም ቀን የዳን ልጆች አለቃ የአሚሳዳይ ልጅ አኪዔዘር፤ [67] መባውም ለእህል ቍርባን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ፥ ሚዛኑ እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ወጭት፥ ሚዛኑም ሰባ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ድስት፤ [68] ዕጣንም የተሞላ ሚዛኑ አሥር ሰቅል የሆነ አንድ የወርቅ ጭልፋ፤ [69] ለሚቃጠልም መሥዋዕት አንድ ወይፈን፥ አንድ አውራ በግ፥ አንድ የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት፤ [70] ለኃጢአትም መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል፤ [71] ለደኅንነትም መሥዋዕት ሁለት በሬዎች፥ አምስት አውራ በጎች፥ አምስት አውራ ፍየሎች፥ አምስት የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች ነበረ፤ የአሚሳዳይ ልጅ የአኪዔዘር መባ ይህ ነበረ።

[72] በአሥራ አንደኛውም ቀን የአሴር ልጆች አለቃ የኤክራን ልጅ ፋግኤል፤ [73] መባውም ለእህል ቍርባን በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት የተሞሉ፥ ሚዛኑ እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ወጭት፥ ሚዛኑም ሰባ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ድስት፤ [74] ዕጣንም የተሞላ ሚዛኑ አሥር ሰቅል የሆነ አንድ የወርቅ ጭልፋ፤ [75] ለሚቃጠልም መሥዋዕት አንድ ወይፈን፥ አንድ አውራ በግ፥ አንድ የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት፤ [76] ለኃጢአትም መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል፤ [77] ለደኅንነትም መሥዋዕት ሁለት በሬዎች፥ አምስት አውራ በጎች፥ አምስት አውራ ፍየሎች፥ አምስት የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች ነበረ፤ የኤክራን ልጅ የፋግኤል መባ ይህ ነበረ።

[78] በአሥራ ሁለተኛውም ቀን የንፍታሌም ልጆች አለቃ የዔናን ልጅ አኪሬ፤ [79] መባውም ለእህል ቍርባን

ከዛቱዕ ልጆችም፤ ዔሊዮዔናይ፥ ኢልያሴብ፥ ሙታንያ፥ ይሬሞት፥ ዛባድ፥ ዓዚዛ። [28] ከቤባይ ልጆችም፤ ይሆሐናን፥ ሐናንያ፥ ዘባይ፥ አጥላይ። [29] ከባኒ ልጆችም፤ ሜሱላም፥ መሉክ፥ ዓዳያ፥ ያሱብ፥ ሸዓል፥ ራሞት። [30] ከፈሐት ሞዓብ ልጆችም፤ ዓድና፥ ክላል፥ በናያስ፥ መዕሤያ፥ ሙታንያ፥ ባስልኤል፥ ቢንዊ፥ ምናሴ። [31] ከካሪም ልጆችም፤ አልዓዛር፥ ይሺያ፥ መልክያ፥ [32] ሸማያ፥ ስምዖን፥ ብንያም፥ መሉክ፥ ሰማራያ። [33] ከሐሱም ልጆችም፤ መትናይ፥ መተታ፥ ዛባድ፥ ኤሊፋላት፥ ይሬማይ፥ ምናሴ፥ ሰሜኢ። [34] ከባኒ ልጆችም፤ መዕዳይ፥ ዓምራም፥ [35] ኡኤል፥ በናያስ፥ ቤድያ፥ ኬልቅያ [36-37] ወንያ፥ ሜሪሞት፥ ኤልያሴብ፥ መታንያ፥ [38] መትናይ፥ የዕሡ፥ ባኒ፥ ቢንዊ፥ ሰሜኢ፥ [39-40] ሰሌምያ፥ ናታን፥ ዓዳያ፥ መክነድባይ፥ [41] ሴሴይ፥ ሸራይ፥ ኤዝርኤል፥ ሰሌምያ፥ ሰማራያ፥ ሰሎም፥ አማርያ፥ ዮሴፍ። [42-43] ከናባው ልጆችም፤ ይዒኤል፥ መቲትያ፥ ዛባድ፥ ዘቢና፥ ያዳይ፥ ኢዮኤል፥ በናያስ። [44] እነዚህ ሁሉ እንግዶቹን ሚስቶች አግብተው ነበር፤ ከእነዚህም ሚስቶች አያሌዎቹ ልጆችን ወልደው ነበር።

አልተሠሩም ነበር።

5 አምላኬም ታላቆቹንና ሹማምቱን ሕዝቡንም ሰብስቤ እቈጥራቸው ዘንድ በልቤ አደረገ፤ አስቀድመው
የመጡትን ሰዎች የትውልድ መጽሐፋቸውን አገኘሁ፥ በእርሱም እንደዚህ ተጽፎ አገኘሁ። 6 የባቢሎን
ንጉሥ ናቡከደነፆር ከማረካቸው ምርኮኞች ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ይሁዳ ወደ እየከተማቸው
የተመለሱት የአገር ልጆች እነዚህ ናቸው። 7 ከዘሩባቤል፥ ከኢያሱ፥ ከነህምያ፥ ከአዛርያስ፥ ከረዓምያ፥
ከነሐማኒ፥ ከመርዶክዮስ፥ ከበላሳን፥ ከሚስጴሬት፥ ከበጉዋይ፥ ከነሑም፥ ከበዓና ጋር መጡ። 8
የእስራኤልም ሕዝብ ሰዎች ቍጥር ይህ ነው፤ የፋሮስ ልጆች፥ ሁለት ሺህ መቶ ሰባ ሁለት። 9 የሰፋጥያስ
ልጆች ሦስት መቶ ሰባ ሁለት። 10 የኤራ ልጆች፥ ስድስት መቶ አምሳ ሁለት። 11 ከኢያሱና ከኢዮአብ
ልጆች የሆኑ የፈሐት ሞዓብ ልጆች፥ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ አሥራ ስምንት። 12 የኤላም ልጆች፥ ሺህ
ሁለት መቶ አምሳ አራት። 13 የዛቱዕ ልጆች፥ ስምንት መቶ አርባ አምስት። 14 የዘካይ ልጆች፥ ሰባት መቶ
ስድሳ። 15 የቢንዊ ልጆች፥ ስድስት መቶ አርባ ስምንት። 16 የቤባይ ልጆች፥ ስድስት መቶ ሀያ ስምንት። 17
የዓዝጋድ ልጆች፥ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ሀያ ሁለት። 18 የአዶኒቃም ልጆች፥ ስድስት መቶ ስድሳ ሰባት።
19 የበጉዋይ ልጆች፥ ሁለት ሺህ ስድሳ ሰባት። 20 የዓዲን ልጆች፥ ስድስት መቶ አምሳ አምስት። 21
የሕዝቅያስ ወገን የአጤር ልጆች፥ ዘጠና ስምንት። 22 የሐሱም ልጆች፥ ሦስት መቶ ሀያ ስምንት። 23
የቤሳይ ልጆች፥ ሦስት መቶ ሀያ አራት። 24 የሐሪፍ ልጆች፥ መቶ አሥራ ሁለት። 25 የገባዖን ልጆች፥ ዘጠና
አምስት። 26 የቤተ ልሔምና የነጦፋ ሰዎች፥ መቶ ሰማንያ ስምንት። 27 የዓናቶች ሰዎች፥ መቶ ሀያ
ስምንት። 28 የቤትዓዝሞት ሰዎች፥ አርባ ሁለት። 29 የቂርያትይዓሪምና የከፊራ የብኤሮትም ሰዎች፥ ሰባት
መቶ አርባ ሦስት። 30 የራማና የጌባ ሰዎች፥ ስድስት መቶ ሀያ አንድ። 31 የማክማስ ሰዎች፥ መቶ ሀያ
ሁለት። 32 የቤቴልና የጋይ ሰዎች፥ መቶ ሀያ ሦስት። 33 የሁለተኛው ናባው ሰዎች፥ አምሳ ሁለት። 34
የሁለተኛው ኤላም ልጆች፥ ሺህ ሁለት መቶ አምሳ አራት። 35 የካሪም ልጆች፥ ሦስት መቶ ሀያ። 36
የኢያሪኮ ልጆች፥ ሦስት መቶ አርባ አምስት 37 የሎድና የሐዲድ የኦኖም ልጆች፥ ሰባት መቶ ሀያ አንድ። 38
የሴናዓ ልጆች፥ ሦስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ።

39 ካህናቱ፤ ከኢያሱ ወገን የዮዳኤ ልጆች፥ ዘጠኝ መቶ ሰባ ሦስት። 40 የኢሜር ልጆች፥ ሺህ አምሳ
ሁለት። 41 የፋስኮር ልጆች፥ ሺህ ሁለት መቶ አርባ ሰባት። 42 የካሪም ልጆች፥ ሺህ አሥራ ሰባት።

43 ሌዋውያኑ፤ ከሆዳይዋ ወገን የኢያሱና የቀድምኤል ልጆች፥ ሰባ አራት።

44 መዘምራኑ፤ የአሳፍ ልጆች፥ መቶ አርባ ስምንት።

45 በረኞቹ፤ የሰሎም ልጆች፥ የአጤር ልጆች፥ የጤልሞን ልጆች፥ የዓቁብ ልጆች፥ የሐጢጣ ልጆች፥
የሶባይ ልጆች፥ መቶ ሠላሳ ስምንት።

46 ናታኒም፥ የሲሐ ልጆች፥ የሐሡፋ ልጆች፥ 47 የጠብዖት ልጆች፥ የኬራስ ልጆች፥ የሲዓ ልጆች፥ 48
የፋዶን ልጆች፥ የልባና ልጆች፥ 49 የአጋባ ልጆች፥ የሰምላይ ልጆች፥ የሐናን ልጆች፥ የጌዴል ልጆች፥
የጋሐር ልጆች፥ 50 የራያ ልጆች፥ የረአሶን ልጆች፥ የኔቆዳ ልጆች፥ 51 የጋሴም ልጆች፥ የዖዛ ልጆች፥ የፋሴሐ
ልጆች፥ 52 የቤሳይ ልጆች፥ የምዑናውያን ልጆች፥ 53 የንፉሰሲም ልጆች፥ የበቅቡቅ ልጆች፥ የሐቀፋ ልጆች፥
የሐርሑር ልጆች፥ 54 የበስሎት ልጆች፥ የምሒዳ ልጆች፥ የሐርሻ ልጆች፥ 55 የበርቆስ ልጆች፥ የሲሣራ
ልጆች፥ 56 የቴማ ልጆች፥ የንስያ ልጆች፥ የሐጢፋ ልጆች።

አለችው፤ እንደሚያስጸይፍ መብል ሆነብኝ። [8] ልመናዬ ምነው በደረሰልኝ እግዚአብሔርም ምኞቴን ምነው በሰጠኝ [9] እግዚአብሔርም ያደቀኝ ዘንድ እጁንም ለቅቆ ያጠፋኝ ዘንድ ወድዶ ቢሆን ኖሮ [10] መጽናናት በሆነልኝ ነበር፤ በማይራራ ሕመም ሐሤት ባደረግሁ ነበር፥ የቅዱሱን ቃል አልካድሁምና። [11] እጠብቅ ዘንድ ጒልበቴ ምንድር ነው እታገሥም ዘንድ ፍጻሜዬ ምንድር ነው [12] ጒልበቴ የድንጋይ ጒልበት ነውን ሥጋዬስ እንደ ናስ ነውን [13] በውኑ ረድኤት በእኔ እንደሌለ ጥበብም ሁሉ ከእኔ ዘንድ እንደ ተባረረ አይደለምን [14] ሁሉን የሚችለውን የአምላክን መፍራት ለሚተው፥ ለመዛል ለቀረበው ስንኳ ወዳጁ ቸርነትን ሊያሳይ ይገባል። [15] ወንድሞቼ እንደ ፈፋ፥ እንደሚያልፍ ፈፋ ሐሰተኞች ሆኑብኝ። [16] ከበረዶ የተነሣ ደፈረሱ፥ አመዳይም ተሰወረባቸው፤ [17] ፀሐይ በተኰሰች ጊዜ ይደርቃሉ፤ በሙቀትም ጊዜ ከስፍራቸው ይጠፋሉ። [18] በየዳርቻቸውም የሚሄዱ ነጋዴዎች ፈቀቅ ይላሉ፤ ወደ በረሃ ወጥተው ይጠፋሉ። [19] የቴማን ነጋዴዎች ተመለከቱ፥ የሳባ መንገደኞችም ተጠባበቁአቸው። [20] ተስፋ አድርገዋቸው ነበርና አፈሩ፤ ወደዚያ ደረሱ፥ እፍረትም ያዛቸው። [21] አሁንም እናንተ እንደዚሁ ሆናችኋል፤ መከራዬን አይታችሁ ፈራችሁ። [22] በውኑ። አንዳች ነገር አምጡልኝ፤ ወይስ። ከብልጥግናችሁ ስጦታ አቅርቡልኝ፤ [23] ወይስ። ከጠላቴ እጅ አስጥሉኝ፤ ወይስ። ከአስጨናቂው እጅ አድኑኝ አልኋችሁን [24] አስተምሩኝ፥ እኔም ዝም እላለሁ፤ የተሳሳትሁትንም ንገሩኝ። [25] የቅንነት ቃል እንዴት ኃይለኛ ነው የእናንተ ሙግት ግን ምን ይገሥጻል [26] ተስፋ የሌለው ሰው ንግግር እንደ ነፋስ ነውና ቃሌን ትገሥጹ ዘንድ ታስባላችሁን [27] በድሀ አደጉ ላይ ዕጣ ትጣጣላላችሁ፤ ለወዳጃችሁም ጒድጓድ ትቈፍራላችሁ። [28] አሁንም፥ እባካችሁ፥ ወደ እኔ ተመልከቱ፤ በፊታችሁም ሐሰት አልናገርም። [29] እባካችሁ፥ ተመለሱ፤ በደል አይሁን፤ ጽድቁ በዚህ ነገር ነውና አንድ ጊዜ ተመለሱ። [30] በውኑ በአንደበቴ በደል ይገኛልን አፌስ ተንኰልን ይለይ ዘንድ አይችልምን

## ምዕራፍ 7

[1] በምድር ላይ የሰው ሕይወት ብርቱ ሰልፍ አይደለምን ወራቱም እንደ ምንደኛ ወራት አይደለምን [2] አገልጋይ ጥላ እንደሚመኝ፥ ምንደኛም ደመወዙን እንደሚጠብቅ፥ [3] እንዲሁ ዕጣዬ የከንቱ ወራት ሆነብኝ፥ የድካምም ሌሊት ተወሰነችልኝ። [4] በተኛሁ ጊዜ። መቼ እነሣለሁ እላለሁ። ሌሊቱ ግን ይረዝማል፥ እስኪነጋ ድረስም እገለባበጣለሁ። [5] ሥጋዬ ትልና ጓል ለብሶአል፤ ቁርበቴ ያፈከፍካል እንደ ገናም ይመግላል። [6] ዘመኔ ከሸማኔ መወርወርያ ይልቅ ይቸኵላል፥ ያለ ተስፋም ያልቃል። [7] ሕይወቴ እስትንፋስ እንደ ሆነ አስብ፤ ዓይኔ መልካም ነገርን ከእንግዲህ ወዲህ አያይም። [8] የሚያየኝ ሰው ዓይን ከእንግዲህ ወዲህ አያየኝም፤ ዓይንህ በእኔ ላይ ይሆናል፥ እኔም አልገኝም። [9] ደመና ተበትኖ እንደሚጠፋ፥ እንዲሁ ወደ ሲኦል የሚወርድ ዳግመኛ አይወጣም። [10] ወደ ቤቱ ዳግመኛ አይመለስም፥ ስፍራውም ዳግመኛ አያውቀውም። [11] ስለዚህም አፌን አልከለክልም፤ በመንፈሴ ጭንቀትን እናገራለሁ፤ በነፍሴ ምሬት በኀዘን አንጐራጒራለሁ። [12] ጠባቂ ታስነሣብኝ ዘንድ፥ እኔ ባሕር ወይስ አንበሪ ነኝን [13] እኔም። አልጋዬ ያጽናናኛል፥ መኝታዬም የኀዘን እንጒርጒሮዬን ያቀልልኛል ባልሁ ጊዜ፥ [14] አንተ በሕልም ታስፈራራኛለህ፥ በራእይም ታስደነግጠኛለህ፤ [15] ነፍሴም ከአጥንቴ ይልቅ መታነቅንና ሞትን መረጠች። [16] ሕይወቴን ናቅኋት፤ ለዘላለም ልኖር አልወድድም። የሕይወቴ ዘመን እስትንፋስ ነውና ተወኝ። [17] ሰው ምንድር ነው ታከብረው ዘንድ፥ ልብህንስ ትጥልበት ዘንድ፥ [18] ማለዳ ማለዳስ ትጐበኘው ዘንድ፥ ሁልጊዜስ ትፈታተነው ዘንድ [19] የማትተወኝ እስከ መቼ ነው ምራቄንስ እስከውጥ ድረስ የማትለቅቀኝ

ስሕተቴ ከእኔ ጋር ትኖራለች። 5 በእውነትም ብትጓደዱብኝ፥ መዋረዴን በእኔ ላይ ብትከራከሩ፥ 6
እንግዲህ እግዚአብሔር እንደ ገለበጠኝ፥ በመረቡም እንደ ከበበኝ እወቁ። 7 እነሆ፥ ስለ ተደረገብኝ ግፍ
ብጮኽ ማንም አይመልስልኝም፤ አሰምቼም ብጠራ ፍርድ የለኝም። 8 እንዳላልፍ መንገዴን ዘግቶታል፥
በጎዳናዬም ጨለማ አኑሮበታል። 9 ክብሬን ገፈፈኝ፥ ዘውዴንም ከራሴ ላይ ወሰደ። 10 በዚህና በዚያም
አፈረሰኝ፥ እኔም ሄድሁ፤ ተስፋዬንም እንደ ዛፍ ነቀለው፤ 11 ቍጣውንም አነደደብኝ፥ እንደ ጠላቱም
ቈጠረኝ። 12 ሠራዊቱ አብረው መጡ፥ መንገዳቸውንም በላዬ አዘጋጁ፥ በድንኳኔም ዙሪያ ሰፈሩ። 13
ወንድሞቼን ከእኔ ዘንድ አራቀ፥ የሚያውቁኝም አጥብቀው ተለዩኝ። 14 ዘመዶቼ ተቋረጡ፥ ወዳጆቼም
ረሱኝ። 15 ቤተ ሰቦቼና ሴቶች ባሪያዎቼ እንደ መጻተኛ ቈጠሩኝ፤ በዓይናቸውም እንደ እንግዳ ሆንሁ። 16
ባሪያዬን ብጠራ፥ በአፌም ባቈላምጥ አይመልስልኝም። 17 ሚስቴ እስትንፋሴን ጠላች፥ የእናቴም ማኅፀን
ልጆች ልመናዬን ጠሉ። 18 ሕፃናቶች እንኳ አጠቁኝ፤ ብነሣም በእኔ ላይ ይናገራሉ። 19 አማካሪዎቼ ሁሉ
ተጸየፉኝ፤ እኔ የምወድዳቸው በላዬ ተገለበጡ። 20 አጥንቴ ከቍርበቴና ከሥጋዬ ጋር ተጣበቀ፤ ድድ ብቻ
ቀርቶልኝ አመለጥሁ። 21 እናንተ ወዳጆቼ ሆይ፥ ማሩኝ፤ የእግዚአብሔር እጅ መትታኛለችና ማሩኝ። 22
ስለ ምን እናንተ እንደ እግዚአብሔር ታሳድዱኛላችሁ ከሥጋዬስ ስለ ምን አትጠግቡም 23 ምነው አሁን
ቃሌ ቢጻፍ ምነው በመጽሐፍ ውስጥ ቢታተም 24 ምነው በብረት ብርና በእርሳስ በዓለቱ ላይ ለዘላለም
ቢቀረጽ 25 እኔን ግን የሚቤዠኝ ሕያው እንደ ሆነ፥ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም፥ 26 ይህ
ቍርበቴም ከጠፋ በኋላ፥ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ። 27 እኔ ራሴ
አየዋለሁ፥ ዓይኖቼም ይመለከቱታል፥ ከእኔም ሌላ አይደለም። ልቤ በመናፈቅ ዝሎአል። 28 በእውነት።
እንዴት እናሳድደዋለን የነገሩ ሥር በእርሱ ዘንድ ተገኝቶአል ብትሉ፥ 29 ፍርድ እንዳለ ታውቁ ዘንድ ቍጣ
የሰይፍን ቅጣት ያመጣልና ከሰይፍ ፍሩ።

## ምዕራፍ 20

1 ናዕማታዊውም ሶፋር መለሰ እንዲህም አለ። 2 ስለዚህ በውስጤ ስላለው ችኰላ አሳቤ
ትመልስልኛለች። 3 የሚያሳፍረኝንም ተግሣጽ ሰምቻለሁ፥ የማስተዋሌም መንፈስ ይመልስልኛል። 4 ሰው
በምድር ላይ ከተቀመጠ፥ ከዱሮ ዘመን ጀምሮ፥ 5 የኃጢአተኛ ፉከራ አጭር መሆኑን የዝንጉዎችም ደስታ
ቅጽበት መሆኑን አታውቁምን 6 ከፍታው ወደ ሰማይ ቢወጣ፥ ራሱም እስከ ደመና ቢደርስ፥ 7 እንደ
ፋንድያ ለዘላለም ይጠፋል፤ ያዩትም። ወዴት ነው ይላሉ። 8 እንደ ሕልም ይበርራል፥ እርሱም አይገኝም፤
እንደ ሌሊትም ራእይ ይሰደዳል። 9 ያየችውም ዓይን ዳግመኛ አታየውም፤ ስፍራውም ከእንግዲህ ወዲህ
አይመለከተውም። 10 ልጆቹ ድሆቹን ያቈላምጣሉ፤ እጁ ሀብቱን ይመልሳል። 11 አጥንቶቹ ብላቴንነቱን
ሞልተዋል፤ ነገር ግን ከእርሱ ጋር በመሬት ውስጥ ይተኛል። 12 ክፋት በአፉ ውስጥ ቢጣፍጥ፥ ከምላሱም
በታች ቢሰውረው፥ 13 ቢጠብቀውም ባይተወውም፥ በጕሮሮውም ቢይዘው፥ 14 መብሉ በአንጀቱ ውስጥ
ይገላበጣል፤ እንደ እፉኝትም ሐሞት በውስጡ ይሆናል። 15 የዋጠውን ሀብት ይተፋዋል፤
እግዚአብሔርም ከሆዱ ውስጥ ያወጣዋል። 16 የእፉኝትን መርዝ ይጠባል፤ የእባብም ምላስ ይገድለዋል።
17 የማሩንና የቅቤውን ፈሳሽ ወንዞቹንም አይመለከትም። 18 የድካሙን ፍሬ ሳይውጠው ይመልሰዋል፤
እንደ ንግዱም ትርፍ አይደሰትም። 19 ድሀውን አስጨንቆአል፥ ትቶታልም፤ ያልሠራውንም ቤት
በዝብዞአል። 20 ሆዱ ዕረፍትን አላወቀምና የወደደው ነገር አላዳነውም። 21 እርሱ ከበላ በኋላ ምንም
አልተረፈም፤ ስለዚህ በረከቱ አይከናወንለትም። 22 በጠገበ ጊዜ ይጨነቃል፤ የችግረኞችም ሁሉ እጅ

ታገኘዋለች። 23 ሆዱን ሳያጠግብ እግዚአብሔር የቍጣውን ትኵሳት ይሰድድበታል፥ ሲበላም
ያዘንብበታል። 24 ከብረት መሣርያም ይሸሻል፥ የናስም ቀስት ይወጋዋል። 25 እርሱም ይመዝዘዋል፥
ከሥጋውም ይወጣል፤ ከሐሞቱም ብልጭ ብሎ ይሠርጻል፤ ፍርሃትም ይወድቅበታል። 26 ጨለማ ሁሉ
ስለ ከበረው ዕቃ ተዘጋጅቶአል፤ በሰው አፍ እፍ የማትባል እሳት ትበላዋለች፤ በድንኳኑ ውስጥ የቀረው
ይጨነቅባታል። 27 ሰማይ ኃጢአቱን ይገልጥበታል፥ ምድርም ትነሣበታለች። 28 የቤቱም ባለጠግነት
ይሄዳል፤ በቍጣው ቀን እንደ ፈሳሽ ውኃ ያልፋል። 29 ከእግዚአብሔር ዘንድ የበደለኛ ሰው እድል ፈንታ፥
ከእግዚአብሔርም የተመደበ ርስቱ ይህ ነው።

# ምዕራፍ 21

1 ኢዮብም መለሰ እንዲህም አለ። 2 ስሙ፥ ቃሌን ስሙ፤ ይህም መጽናናታችሁ ይሁን። 3 እናገር ዘንድ
ተዉኝ፤ ከተናገርሁም በኋላ ተሳለቁ። 4 በውኑ የኀዘን እንጕርጕሮዬ ለሰው እናገራለሁን አለመታገሥ ስለ
ምን አይገባኝም 5 ወደ እኔ ተመልከቱ፥ ተደነቁም፤ እጃችሁንም በአፋችሁ ላይ አኑሩ። 6 እኔ ባሰብሁ
ቍጥር እጨነቃለሁ፥ ፃዕርም ሥጋዬን ይይዛል። 7 ስለ ምን ኃጢአተኞች በሕይወት ይኖራሉ ስለ ምንስ
ያረጃሉ በባለጠግነትስ ስለ ምን ይበረታሉ 8 ዘራቸው ከእነርሱ ጋር ጸንቶ ይኖራል፥ ልጆቻቸውም
በዓይናቸው ፊት ናቸው። 9 ቤታቸው ከፍርሃት ወጥቶ የታመነ ነው፥ የእግዚአብሔርም በትር
የለባቸውም። 10 ኮርማቸው ይወልዳል፥ ዘሩንም አይጥለውም፤ ላማቸውም ትወልዳለች፥ አትጨነግፍም።
11 ሕፃናቶቻቸውን እንደ መንጋ ያወጣሉ፥ ልጆቻቸውም ይዘፍናሉ። 12 ከበሮና መሰንቆ ወስደው
ይዘምራሉ፥ በእምቢልታ ድምፅ ደስ ይላቸዋል። 13 ዕድሜያቸውንም በተድላ ይፈጽማሉ፤ ድንገትም ወደ
ሲኦል ይወርዳሉ። 14 እግዚአብሔርንም። ከእኛ ዘንድ ራቅ፤ መንገድህን እናውቅ ዘንድ አንወድድም። 15
እናመልከውስ ዘንድ ሁሉን የሚችል አምላክ ማን ነው ወይስ ወደ እርሱ ብንጸልይ ምን ይጠቅመናል
ይላሉ። 16 እነሆ፥ ሀብታቸው በእጃቸው ውስጥ አይደለምን የኃጥአን ምክር ከእኔ ዘንድ የራቀች ናት። 17
የኃጥአን መብራት የጠፋው፥ መቅሠፍትም የመጣባቸው፥ እግዚአብሔርም በቍጣው መከራ
የከፈላቸው፥ 18 በነፋስ ፊት እንደ ገለባ፥ ዐውሎ ነፋስም እንደሚወስደው ትቢያ የሆኑ ስንት ጊዜ ነው 19
እናንተ። እግዚአብሔር በደላቸውን ለልጆቻቸው ይጠብቃል ብላችኋል። እነርሱ ያውቁ ዘንድ ፍዳን
ለራሳቸው ይክፈል። 20 ዓይኖቻቸው ጥፋታቸውን ይዩ፥ ሁሉን ከሚችል አምላክ ቍጣ ይጠጡ። 21
የወራታቸውስ ቍጥር ቢቈረጥ፥ ከእነርሱ በኋላ የቤታቸው ደስታ ምን ይሆናቸዋል 22 ከፍ ከፍ ባሉትስ
ላይ ለሚፈርድ ለእግዚአብሔር በውኑ ሰው እውቀትን ያስተምራልን 23 አንድ ሰው በሰላም ተዘልሎ
ሲቀመጥ በሙሉ ኃይሉ ሳለ ይሞታል። 24 በአንጀቱ ውስጥ ስብ ሞልቶአል፥ የአጥንቶቹም ቅልጥም
ረጥቦአል። 25 ሌላውም ሰው መልካምን ነገር ከቶ ሳይቀምስ በተመረረች ነፍስ ይሞታል። 26 በአፈር
ውስጥ በአንድ ላይ ይተኛሉ፥ ትልም ይከድናቸዋል። 27 እነሆ፥ አሳባችሁን፥ የመከራችሁብኝንም ክፉ
ምክር አውቄዋለሁ። 28 እናንተ። የከበርቴው ቤት የት ነው ኃጢአተኛውም ያደረበት ድንኳን የት ነው
ብላችኋል። 29 መንገድ አላፊዎችን አልጠየቃችሁምን ምልክታቸውን አታውቁምን 30 ኃጢአተኛው
በመቅሠፍት ቀን እንደ ተጠበቀ፥ በቍጣው ቀን እንደሚድን። 31 መንገዱን በፊቱ የሚናገር ማን ነው
የሠራውንስ የሚመልስበት ማን ነው 32 እርሱን ግን ወደ መቃብር ይሸከሙታል፥ ሰዎቹም በመቃብሩ
ላይ ይጠብቃሉ። 33 የሸለቆው ጓል ይጣፍጥለታል፤ በኋላውም ሰው ሁሉ ይሳባል፥ በፊቱም ቍጥር
የሌለው ጉባኤ አለ። 34 የምትመልሱልኝ ውስልትና ነውና በከንቱ እንዴት ታጽናኑኛላችሁ

# ምዕራፍ 22

1 ቴማናዊውም ኤልፋዝ መለሰ እንዲህም አለ። 2 በውኑ ሰው እግዚአብሔርን ይጠቅመዋልን በእውነት
ጥበበኛ ሰው ራሱን ይጠቅማል። 3 ጻድቅ መሆንህስ ሁሉን የሚችለውን አምላክ ደስ ያሰኘዋልን
መንገድህን ማቅናትህስ ይጠቅመዋልን 4 እርሱንስ ስለ ፈራህ ይዘልፍሃልን ወደ ፍርድስ ከአንተ ጋር
ይገባልን 5 ክፋትህስ የበዛ አይደለምን ለኃጢአትህም ፍጻሜ የላትም። 6 የወንድሞችህን መያዣ በከንቱ
ወስደሃል፥ የእርዘኞቹንም ልብስ ዘርፈሃል። 7 ለደካማ ውኃ አላጠጣህም፥ ለራብተኛም እንጀራን
ከልክለሃል። 8 በክንድ የበረታ ምድርን ገዛ፤ ከበርቴውም ሰው ተቀመጠባት። 9 መበለቲቱን አንዳች አልባ
ሰድደሃታል፤ የድሀ አደጎችም ክንድ ተሰብሮአል። 10 ስለዚህ አሽክላ ከብቦሃል፥ ድንገተኛ ፍርሃትም
አናውጦሃል። 11 እንዳታይ ብርሃን ጨለማ ሆነችብህ፥ የውኆችም ብዛት አሰጠመህ። 12 እግዚአብሔር
በሰማያት ከፍ ከፍ አይልምን ከዋክብትም እንዴት ከፍ ከፍ እንዳሉ ተመልከት። 13 አንተም።
እግዚአብሔር ምን ያውቃል በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ሆኖ ሊፈርድ ይችላልን 14 እንዳያይ የጠቈረ
ደመና ጋርዶታል፤ በሰማይ ክበብ ላይ ይራመዳል ብለሃል። 15 በውኑ ኃጢአተኞች ሰዎች የረገጡአትን
የዱሮይቱን መንገድ ትጠብቃለህን 16 ጊዜያቸው ሳይደርስ ተነጠቁ፤ መሠረታቸውም እንደ ፈሳሽ ውኃ
ፈሰሰ። 17 እግዚአብሔርንም። ከእኛ ዘንድ ራቅ፤ ሁሉንም የሚችል አምላክ ምን ሊያደርግልን ይችላል
አሉት። 18 ነገር ግን ቤታቸውን በመልካም ነገር ሞላ፤ የኃጥአን ምክር ከእኔ ዘንድ የራቀች ናት። 19
ጻድቃን ያዩታል፥ ደስም ይላቸዋል፤ ንጹሐንም በንቀት ይስቁባቸዋል። 20 በእውነት ሀብታቸው ጠፋ፥
የቀረውንም እሳት በላች። 21 አሁንም ከእርሱ ጋር ተስማማ፥ ሰላምም ይኑርህ፤ በዚያም በጎነት ታገኛለህ።
22 ከአፉም ሕጉን ተቀበል፥ በልብህም ቃሉን አኑር፤ 23 ሁሉን ወደሚችል አምላክ ብትመለስ፥
ብትዋረድም፥ ኃጢአትንም ከድንኳንህ ብታርቅ፥ 24 የወርቅን ዕቃ በአፈር ውስጥ፥ የኦፊርንም ወርቅ
በጅረት ድንጋይ መካከል ብትጥል፥ 25 ሁሉን የሚችል አምላክ ወርቅና የሚብለጨለጭ ብር ይሆንልሃል።
26 የዚያን ጊዜ ሁሉን በሚችል አምላክ ደስ ይልሃል፥ ፊትህንም ወደ እግዚአብሔር ታነሣለህ። 27 ወደ
እርሱም ትጸልያለህ፥ እርሱም ይሰማሃል፤ ስእለትህንም ትሰጣለህ። 28 ነገርንም ትመክራለህ፥ እርሱም
ይሳካልሃል፤ ብርሃንም በመንገድህ ላይ ይበራል። 29 ቢያዋርዱህ አንተ ከፍ ከፍ ትላለህ፤ ትሑቱንም ሰው
ያድነዋል። 30 ንጹሑን ሰው ያድነዋል፤ በእጅህም ንጽሕና ትድናለህ።

# ምዕራፍ 23

1 ኢዮብም መለሰ እንዲህም አለ። 2 ዛሬም ደግሞ የኀዘን እንጕርጕሮዬ ገና መራራ ነው፤ እጁ በልቅሶ
ጩኸቴ ላይ ከብዳለች። 3 እርሱን ወዴት እንዳገኘው ምነው ባወቅሁ ወደ ተቀመጠበትስ ስፍራ ምነው
በደረስሁ 4 በፊቱ ሙግቴን አዘጋጅ ነበር፥ አፌንም በማስረጃ እሞላው ነበር። 5 የሚመልስልኝም ቃል ምን
እንደ ሆነ አውቅ ነበር፥ የሚለኝንም አስተውል ነበር። 6 በኃይሉ ብዛት ከእኔ ጋር ይምዋገት ነበርን እንኳን
ያደምጠኝ ነበር። 7 ቅን ሰው ከእርሱ ጋር በዚያ ይከራከር ነበር፤ እኔም ከፈራጄ ለዘላለም እድን ነበር። 8
እነሆ፥ ወደ ፊት እሄዳለሁ፥ እርሱም የለም፤ ወደ ኋላም እሄዳለሁ፥ እኔም አላስተውለውም፤ 9
ወደሚሠራበት ወደ ግራ ብሄድ አልመለከተውም፤ በቀኝም ይሰወራል፥ አላየውምም፤ 10 የምሄድበትን
መንገድ ያውቃል፤ ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ። 11 እግሬ ወደ እርምጃው ተጣብቆአል፤
መንገዱንም ጠብቄአለሁ፥ ፈቀቅም አላልሁም። 12 ከከንፈሩ ትእዛዝ አልተመለስሁም፤ የአፉን ቃል በልቤ

ይበልጥ አይመለከትም። [20] እነርሱ በመንፈቀ ሌሊት በድንገት ይሞታሉ፤ ሕዝቡ ተንቀጥቅጦ ያልፋል፥ ኃያላንም ያለ እጅ ይነጠቃሉ። [21] ዓይኖቹ በሰው መንገድ ላይ ናቸው፥ እርምጃውንም ሁሉ ያያል። [22] ኃጢአትን የሚሠሩ ይሰወሩበት ዘንድ ጨለማ ወይም የሞት ጥላ የለም። [23] ሰው በእግዚአብሔር ፊት ለመፈራረድ እንዲመጣ ጊዜ አይወስንለትም። [24] ታላላቆችን ያለ ምርመራ ይሰባብራል፥ በእነርሱም ፋንታ ሌሎችን ያቆማል። [25] ሥራቸውን ያውቃል፤ እንዲደቅቁም በሌሊት ይገለባብጣቸዋል። [26] ሰዎች እያዩ እንደ ክፉዎች ይመታቸዋል፤ [27-28] የድሀውን ልቅሶ ወደ እርሱ ያደርሱ ዘንድ፥ እርሱም የችግረኛውን ድምፅ ይሰማ ዘንድ፥ እርሱን ከመከተል ፈቀቅ ብለዋልና፥ ከመንገዱም ሁሉ አንዱን አልተመለከቱምና። [29] በሕዝብ ወይም በሰው ዘንድ ቢሆን፥ እርሱ ቢያሳርፍ የሚፈርድ ማን ነው ፊቱንስ ቢሰውር የሚያየው ማን ነው [30] ይህም ዝንጉ ሰው እንዳይነግሥ፥ ሕዝቡም የሚያጠምድ እንዳይኖር ነው። [31] እግዚአብሔርን። እኔ ሳልበድል ቅጣት ተቀበልሁ፤ [32] የማላየውን ነገር አንተ አስተምረኝ፤ ኃጢአትንም ሠርቼ እንደ ሆነ፥ ደግሜ አልሠራም የሚለው ማን ነው [33] በውኑ አንተ ጥለኸዋልና ፍዳው አንተ እንደምትወድደው ይሆናልን አንተ ትመርጣለህ እንጂ እኔ አይደለሁም፤ ስለዚህ የምታውቀውን ተናገር። [34] የሚሰሙኝ ጥበበኞች ሁሉ፥ አስተዋዮችም እንዲህ ይሉኛል። [35] ኢዮብ ያለ እውቀት ተናግሮአል፥ ቃሉም በአእምሮ አይደለችም። [36] ኢዮብ እስከ ፍጻሜ ድረስ ምነው በተፈተነ ኖሮ እርሱ እንደ ክፉዎች መልሶአልና፤ [37] በኃጢአቱም ላይ ዓመፅን ጨምሮአልና፥ በእኛም መካከል በእጁ ያጨበጭባልና፥ ቃልንም በእግዚአብሔር ላይ ያበዛልና።

## ምዕራፍ 35

[1] ኤሊሁም ደግሞ መለሰ እንዲህም አለ። [2] ይህ ጽድቅ እንደ ሆነ ታስባለህን ወይስ። በእግዚአብሔር ፊት እኔ ጻድቅ ነኝ ትላለህን [3] አንተ። ምን ጥቅም አለህ ኃጢአት ሠርቼ ከማገኘው ይልቅ ኃጢአት ባልሠራ ኖሮ ምን እጠቀማለሁ ብለህ ጠይቀሃልና። [4] እኔ ለአንተና ከአንተ ጋር ላሉ ለባልንጀሮችህ እመልሳለሁ። [5] ዓይኖችህን ወደ ሰማይ አቅንተህ እይ፤ ከአንተም ከፍ ከፍ ያሉትን ደመናት ተመልከት። [6] ኃጢአት ብትሠራ ምን ትጐዳዋለህ መተላለፍህስ ቢበዛ ምን ታደርገዋለህ [7] ጻድቅስ ብትሆን ምን ትሰጠዋለህ ወይስ ከእጅህ ምንን ይቀበላል [8] እንደ አንተ ያለውን ሰው ክፋትህ ይጐዳዋል፤ ለሰውም ልጅ ጽድቅህ ይጠቅመዋል። [9] ከግፍ ብዛት የተነሣ ሰዎች ይጮኻሉ፤ ከኃያላንም ክንድ የተነሣ ለእርዳታ ይጠራሉ። [10-11] ነገር ግን። በሌሊት መዝሙርን የሚሰጥ፥ ከምድርም እንስሶች ይልቅ የሚያስተምረን ከሰማይም ወፎች ይልቅ ጥበበኞች የሚያደርገን፤ ፈጣሪዬ እግዚአብሔር ወዴት ነው የሚል የለም። [12] በዚያ ስለ ክፉ ሰዎች ትዕቢት ይጮኻሉ፥ እርሱ ግን አይመልስላቸውም። [13] በእውነት እግዚአብሔር ከንቱ ነገርን አይሰማም፥ ሁሉን የሚችል አምላክም አይመለከተውም፤ [14] ይልቁንም። አላየውም፤ ነገሩ በእርሱ ፊት ነው፥ እኔም አጠብቀዋለሁ ስትል። [15] አሁን ግን በቍጣው አልጐበኘምና። በኃጢአት እጅግ አያስብም ትላለህ። [16] ስለዚህ ኢዮብ አፉን በከንቱ ይከፍታል፥ ያለ እውቀትም ቃሉን ያበዛል።

## ምዕራፍ 36

[1] ኤሊሁም ደግሞ መለሰ እንዲህም አለ። [2] ገና ስለ እግዚአብሔር የሚነገር አለኝና ጥቂት ቆየኝ፥ እኔም

ይጐበኛል፤ ዓይኑም በሩቅ ትመለከታለች። [30] ጫጬቶቹም ደም ይጠጣሉ፤ በድን ባለባትም ስፍራ እርሱ
በዚያ አለ።

## ምዕራፍ 40

[1] እግዚአብሔርም መለሰ ኢዮብንም እንዲህ አለው። [2] በውኑ የሚከራከር ሰው ሁሉን ከሚችል አምላክ
ጋር ይከራከራልን ከእግዚአብሔር ጋር የሚዋቀስ እርሱ ይመልስለት።

[3] ኢዮብም መለሰ እግዚአብሔርንም እንዲህ አለው። [4] እነሆ፥ እኔ ወራዳ ሰው ነኝ፤ የምመልስልህ
ምንድር ነው እጄን በአፌ ላይ እጭናለሁ። [5] አንድ ጊዜ ተናገርሁ፥ አልመልስምም፤ ሁለተኛ ጊዜም፥
ከእንግዲህ ወዲህ አልናገርም።

[6] እግዚአብሔርም በዐውሎ ነፋስ ውስጥ ሆኖ ለኢዮብ መለሰ እንዲህም አለ። [7] እንግዲህ እንደ ወንድ
ወገብህን ታጠቅ፤ እጠይቅሃለሁ፥ አንተም ተናገረኝ። [8] በውኑ ፍርዴን ታፈርሳለህን አንተስ ጻድቅ ትሆን
ዘንድ በእኔ ትፈርዳለህን [9] እንደ እግዚአብሔር ክንድ ያለ ክንድ አለህን ወይስ እንደ እርሱ ባለ ድምፅ
ታንጐደጕዳለህን [10] በታላቅነትና በልዕልና ተላበስ፤ በክብርና በግርማም ተጐናጸፍ። [11] የቍጣህን ፈሳሽ
አፍስስ፤ ትዕቢተኛውንም ሁሉ ተመልክተህ አዋርደው። [12] ትዕቢተኛውንም ሁሉ ተመልከት፥ ዝቅ ዝቅም
አድርገው፤ በደለኞችንም ወዲያውኑ እርገጣቸው። [13] በአፈር ውስጥ በአንድነት ሰውራቸው፤ በተሸሸገም
ስፍራ ፊታቸውን ሸፍን። [14] በዚያን ጊዜም ቀኝ እጅህ ታድንህ ዘንድ እንድትችል እኔ ደግሞ
እመሰክርልሃለሁ።

[15] ከአንተ ጋር የሠራሁትን ጉማሬ፥ እስኪ፥ ተመልከት፤ እንደ በሬ ሣር ይበላል። [16] እነሆ፥ ብርታቱ
በወገቡ ውስጥ ነው፤ ኃይሉም በሆዱ ጅማት ውስጥ ነው። [17] ጅራቱን እንደ ጥድ ዛፍ ያወዛውዛል፤
የወርቹ ጅማት የተጐነጐነ ነው። [18] አጥንቱ እንደ ናስ አገዳ ነው፤ አካላቱ እንደ ብረት ዘንጎች ናቸው። [19]
እርሱ የእግዚአብሔር ፍጥረት አውራ ነው፤ ሠሪውም ሰይፉን ሰጠው። [20] የሜዳ እንስሶች ሁሉ
የሚጫወቱበት ተራራ ምግብን ያበቅልለታል። [21] ጥላ ካለው ዛፍ በታች፥ በደንገልና በረግረግ ውስጥ
ይተኛል። [22] ጥላ ያለው ዛፍ በጥላው ይሰውረዋል፤ የወንዝ አኻያ ዛፎች ይከብቡታል። [23] እነሆ፥ ወንዙ
ቢጐርፍ አይደነግጥም፤ ዮርዳኖስም እስከ አፉ ድረስ ቢፈስስ እርሱ ይተማመናል። [24] ዓይኖቹ እያዩ
ይያዛልን አፍንጫውስ በወጥመድ ይበሳልን [25] በውኑ አዞውን በመቃጥን ታወጣለህን ምላሱንስ በገመድ
ታስረዋለህን [26] ወይስ ስናጋ በአፍንጫው ታደርጋለህን ወይስ በችንካር ጕንጩን ትበሳለህን [27] በውኑ ወደ
አንተ እጅግ ይለምናልን በጣፈጠስ ቃል ይናገርሃልን [28] በውኑ ከአንተ ጋር ቃል ኪዳን ይገባልን ወይስ
ለዘላለም ባሪያ ታደርገዋለህን [29] ከወፍ ጋር እንደምትጫወት ከእርሱ ጋር ትጫወታለህን ወይስ ለሴት
ባሪያዎችህ ታስረዋለህን [30] አጥማጆች በእርሱ ይከራከራሉን ወይስ ነጋዴዎች ያካፍሉታልን [31] በውኑ
ቁርበቱን በጭሬ፥ ራሱንስ በዓሣ ጦር ትሞላዋለህን [32] እጅህን በላዩ ጫን፤ ሰልፉን አስብ፥ እንግዲህም
አትድገም።

## ምዕራፍ 41

## ምዕራፍ 2

1 ልጄ ሆይ፥ ቃሌን ብትቀበል፥ ትእዛዜንም በአንተ ዘንድ ሸሽገህ ብትይዛት፥ 2 ጆሮህ ጥበብን
እንዲያደምጥ ታደርጋለህ፥ ልብህንም ወደ ማስተዋል ታዘነብላለህ። 3 ረቂቅ እውቀትን ብትጠራት፥
ለማስተዋልም ድምፅህን ብታነሣ፥ 4 እርስዋንም እንደ ብር ብትፈላልጋት፥ እርስዋንም እንደ ተቀበረ
ገንዘብ ብትሻት፤ 5 የዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን መፍራት ታውቃለህ፥ የአምላክንም እውቀት ታገኛለህ። 6
እግዚአብሔር ጥበብን ይሰጣልና፤ ከአፉም እውቀትና ማስተዋል ይወጣሉ፤ 7 እርሱ ለቅኖች ደኅንነትን
ያከማቻል፤ ያለ ነውር ለሚሄዱትም ጋሻ ነው፤ 8 የፍርድን ጎዳና ይጠብቃል፤ የቅዱሳኑንም መንገድ
ያጸናል። 9 የዚያን ጊዜ ጽድቅንና ፍርድን ቅንነትንና መልካም መንገድን ሁሉ ታስተውላለህ።

10 ጥበብ ወደ ልብህ ትገባለችና፥ እውቀትም ነፍስህን ደስ ታሰኛለችና፤ 11 ጥንቃቄ ይጠብቅሃል፥
ማስተዋልም ይጋርድሃል፥ 12 ከክፉ መንገድ አንተን ለማዳን፥ ጠማማ ነገርን ከሚናገሩም ሰዎች፤ 13
እነርሱም በጨለማ መንገድ ይሄዱ ዘንድ የቀናውን ጎዳና የሚተው፥ 14 ክፉ በመሥራት ደስ የሚላቸው
በጠማማነትም ደስታን የሚያደርጉ፥ 15 መንገዳቸውን የሚጠመዝዙ አካሄዳቸውንም የሚያጣምሙ
ናቸው፤ 16 ከጋለሞታ ሴት አንተን ለመታደግ፥ ቃልዋን ከምታለዝብ ከሌላዪቱም ሴት፤ 17 የሕፃንነት
ወዳጅዋን የምትተው የአምላክዋንም ቃል ኪዳን የምትረሳ፤ 18 ቤትዋ ወደ ሞት ያዘነበለ ነው፥
አካሄድዋም ወደ ሙታን ጥላ። 19 ወደ እርስዋ የሚገቡ ሁሉ አይመለሱም፥ የሕይወትንም ጎዳና
አያገኙም፤ 20 አንተም በደጋግ ሰዎች መንገድ እንድትሄድ የጻድቃንንም ጎዳና እንድትጠብቅ። 21 ቅኖች
በምድር ላይ ይቀመጣሉና፥ ፍጹማንም በእርስዋ ይኖራሉና፤ 22 ኃጥኣን ግን ከምድር ይጠፋሉ፥
ዓመፀኞችም ከእርስዋ ይነጠቃሉ።

## ምዕራፍ 3

1 ልጄ ሆይ፥ ሕጌን አትርሳ፥ ልብህም ትእዛዛቴን ይጠብቅ። 2 ብዙ ዘመናትና ረጅም ዕድሜ ሰላምም
ይጨምሩልሃልና። 3 ምሕረትና እውነት ከአንተ አይራቁ፤ በአንገትህ እሰራቸው፤ በልብህ ጽላት ጻፋቸው።
4 በእግዚአብሔርና በሰው ፊትም ሞገስንና መልካም ዝናን ታገኛለህ።

5 በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤ 6 በመንገድህ ሁሉ እርሱን
እወቅ፥ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል።

7 በራስህ አስተያየት ጠቢብ አትሁን፤ እግዚአብሔርን ፍራ፥ ከክፋትም ራቅ፤ 8 ይህም ለሥጋህ ፈውስ
ይሆንልሃል፥ ለአጥንትህም ጠገን። 9 እግዚአብሔርን ከሀብትህ አክብር፥ ከፍሬህም ሁሉ በኵራት፤ 10
ጐተራህም እህልን ይሞላል፥ መጥመቂያህም በወይን ጠጅ ሞልታ ትትረፈረፋለች።

11 ልጄ ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አትናቅ፥ በገሠጸህም ጊዜ አትመረር። 12 እግዚአብሔር
የወደደውን ይገሥጻልና፥ አባት የሚወድደውን ልጁን እንደሚገሥጽ።

13 ጥበብን የሚያገኝ ሰው ምስጉን ነው፥ ማስተዋልንም ገንዘቡ የሚያደርግ፤ 14 በወርቅና በብር ከመነገድ
ይልቅ በእርስዋ መነገድ ይሻላልና። 15 ከቀይ ዕንቍም ትከብራለች፥ የተከበረም ነገር ሁሉ

እንደሚሰናከሉም አያውቁም።

20 ልጄ ሆይ፥ ንግግሬን አድምጥ ወደ ቃሌም ጆሮህን አዘንብል። 21 ከዓይንህ አታርቃት፥ በልብህም
ውስጥ ጠብቃት። 22 ለሚያገኙአት ሕይወት፥ ለሥጋቸውም ሁሉ ፈውስ ነውና።

23 አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና። 24 የአፍህን ጠማማነት ከአንተ አውጣ፥
ሐሰተኞቹን ከንፈሮችም ከአንተ አርቅ። 25 ዓይኖችህ አቅንተው ይዩ፥ ሽፋሽፍቶችህም በቀጥታ
ይመልከቱ። 26 የእግርህን መንገድ አቅና፥ አካሄድህም ሁሉ ይጽና። 27 ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል፤
እግርህንም ከክፉ መልስ።

# ምዕራፍ 5

1 ልጄ ሆይ፥ ወደ ጥበቤ አድምጥ፤ ጆሮህን ወደ ትምህርቴ መልስ፥ 2 ጥንቃቄን ትጠብቅ ዘንድ
ከንፈሮችህም እውቀትን እንዲጠብቁ።

3 ከጋለሞታ ሴት ከንፈር ማር ይንጠባጠባልና፥ አፍዋም ከቅቤ የለሰለሰ ነውና፤ 4 ፍጻሜዋ ግን እንደ
እሬት የመረረ ነው፥ ሁለት አፍ እንዳለው ሰይፍም የተሳለ ነው። 5 እግሮችዋ ወደ ሞት ይወርዳሉ፥
አረማመድዋም ወደ ሲኦል ነው፤ 6 የቀና የሕይወትን መንገድ አታገኝም፤ በአካሄድዋ የተቅበዘበዘች ናት፥
የሚታወቅም አይደለም። 7 አሁንም ልጆቼ ሆይ፥ ስሙኝ፥ ከአፌም ቃል አትራቁ። 8 መንገድህን ከእርስዋ
አርቅ፥ ወደ ቤትዋም ደጅ አትቅረብ፥ 9 ክብርህ ለሌላ እንዳትሰጥ፥ ዕድሜህም ለጨካኝ፤ 10 ሌሎች
ከሀብትህ እንዳይጠግቡ፥ ድካምህም በባዕድ ሰው ቤት እንዳይሆን። 11 በመጨረሻም ሥጋህና ሰውነትህ
በጠፉ ጊዜ ታለቅሳለህ፥ 12 ትላለህም። እንዴት ትምህርትን ጠላሁ፥ ልቤም ዘለፋን ናቀ 13
የአስተማሪዎቼንም ቃል አልሰማሁም፥ ጆሮቼንም ወደ አስተማሪዎቼ አላዘነበልሁም። 14 በማኅበርና
በጉባኤ መካከል ወደ ክፉ ሁሉ ለመድረስ ጥቂት ቀረኝ።

15 ከጉድጓድህ ውኃ፥ ከምንጭህም የሚፈልቀውን ውኃ ጠጣ። 16 ምንጮችህ ወደ ሜዳ፥ ወንዞችህ ወደ
አደባባይ፥ ይፈስሳሉን 17 ለአንተ ብቻ ይሁኑ፥ ከአንተ ጋር ላሉ እንግዶችም አይሁኑ። 18 ምንጭህ ቡሩክ
ይሁን፤ ከጕብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ። 19 እንደ ተወደደች ዋላ እንደ ተዋበችም ሚዳቋ፥ ጡትዋ
ሁልጊዜ ታርካህ፥ በፍቅርዋም ሁልጊዜ ጥገብ። 20 ልጄ ሆይ፥ ስለ ምን ጋለሞታ ሴት ትወድዳለህ
የሌላይቱንስ ብብት ለምን ታቅፋለህ 21 የሰው መንገድ በእግዚአብሔር ፊት ነውና፥ አካሄዱንም ሁሉ
እርሱ ይመለከታልና።

22 ኃጥኣንን ኃጢአቱ ታጠምደዋለች፥ በኃጢአቱም ገመድ ይታሰራል። 23 አልተቀጣምና እርሱ ይሞታል፤
በስንፍናውም ብዛት ይስታል።

# ምዕራፍ 6

1 ልጄ ሆይ፥ ለጎረቤትህ ዋስ ብትሆን፥ ስለ ሌላ ሰው እጅህን አጋና ብትመታ፥ 2 በአፍህ ቃል ተጠመድህ፤
በአፍህ ቃል ተያዝህ። 3 ልጄ ሆይ፥ ይህን አድርግ ራስህንም አድን፥ በጎረቤትህ እጅ ወድቀሃልና፤ ፈጥነህ

የቤትዋን መንገድ ይዞ ወደ እርስዋ አቀና፥ [9] ማታ ሲመሽ፥ ውድቅትም ሲሆን፥ በሌሊትም በጽኑ ጨለማ።
[10] እነሆ፥ ሴት ተገናኘችው የጋለሞታ ልብስ የለበሰች፥ ነፍሳትን ለማጥመድ የተዘጋጀች። [11] ሁከተኛና
አባያ ናት፥ እግሮችዋም በቤትዋ አይቀመጡም፤ [12] አንድ ጊዜ በጎዳና፥ አንድ ጊዜ በአደባባይ፥ በማዕዘኑም
ሁሉ ታደባለች። [13] ያዘችውም ሳመችውም፤ ፊትዋም ያለ እፍረት ሆኖ እንዲህ አለችው። [14]
መሥዋዕትንና የደኅንነት ቍርባንን ማቅረብ ነበረብኝ፤ ዛሬ ስእለቴን ፈጸምሁ። [15] ስለዚህ እንድገናኝህ፥
ፊትህንም በትጋት ለመሻት ወጥቻለሁ፥ አግኝቼሃለሁም። [16] በአልጋዬ ላይ ማለፊያ ሰርፍ ዘርግቼበታለሁ፥
የግብጽንም ሽመልመሌ ለሀፍ። [17] በመኝታዬ ከርቤንና ዓልሙን ቀረፋም ረጭቼበታለሁ። [18] ና፥ እስኪነጋ
ድረስ በፍቅር እንርካ፥ በተወደደ መተቃቀፍም ደስ ይበለን። [19] ባለቤቴ በቤቱ የለምና፥ ወደ ሩቅ መንገድ
ሄዶአልና፤ [20] በእጁም የብር ከረጢት ወስዶአል፤ሙሉ ጨረቃ በሆነች ጊዜ ወደ ቤቱ ይመለሳል። [21]
በብዙ ጨዋታዋ እንዲስት ታደርገዋለች፤ በከንፈርዋ ልዝብነት ትጐትተዋለች። [22] እርሱ እንዲህ ስቶ
ይከተላታል፥ በሬ ለመታረድ እንዲነዳ፥ ውሻም ወደ እስራት እንዲሄድ፥ [23] ወፍ ወደ ወጥመድ
እንደሚቸኩል፥ ለነፍሱ ጥፋት እንደሚሆን ሳያውቅ፥ ፍላጻ ጉበቱን እስኪሰነጥቀው ድረስ።

[24] ልጆቼ ሆይ፥ አሁን እንግዲህ ስሙኝ ወደ አፌም ቃል አድምጡኝ። [25] ልብህ ወደ መንገድዋ
አያዘንብል በጎዳናዋ አትሳት። [26] ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸውና፤ እርስዋም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ
ናቸው። [27] ቤትዋ የሲኦል መንገድ ነው፤ ወደ ሞት ማጀት የሚወርድ ነው።

## ምዕራፍ 8

[1] በውኑ ጥበብ አትጮኽምን ማስተዋልስ ድምፅዋን አትሰጥምን [2] በኮረብታ ላይ በመንገድ አጠገብ
በጎዳና መካከል ትቆማለች። [3] በበሩ አጠገብ በከተማይቱም መግቢያ፥ በደጁ መግቢያ ትጮኻለች። [4]
እናንተ ሰዎች፥ እናንተን እጠራለሁ፥ ድምፄም ወደ ሰዎች ልጆች ነው። [5] እናንተ አላዋቂዎች፥ ብልሃትን
አስተውሉ፤ እናንተም ሰነፎች ጥበብን በልባችሁ ያዙ። [6] የከበረች ነገርን እናገራለሁና ስሙ፤ ከንፈሮቼም
ቅን ነገርን ለመናገር ይከፈታሉ። [7] አፌ እውነትን ይናገራልና፥ ከንፈሮቼም ክፋትን ይጸየፋሉ። [8] የአፌ
ቃላት ሁሉ ጽድቅ ናቸው፤ ጠማማ ዘወርዋራም አይደሉም። [9] እነርሱ በሚያስተውሉ ዘንድ የቀኑ ናቸው፥
እውቀትንም ካገኙአት ሰዎች ጋር የተስማሙ ናቸው። [10] ተግሣጼን እንጂ ብርን አትቀበሉ፥ ከምዝምዝ
ወርቅም ይልቅ እውቀትን ተቀበሉ። [11] ጥበብ ከቀይ ዕንቍ ትበልጣለችና የከበረ ነገር ሁሉ
አይተካከላትም። [12] እኔ ጥበብ በብልሃት ተቀምጫለሁ፥ እውቀትንም ጥንቃቄንም አግኝቻለሁ። [13]
እግዚአብሔርን መፍራት ክፋትን ይጠላል፤ ትዕቢትንና እብሪትን ክፉንም መንገድ ጠማማውንም አፍ
እጠላለሁ። [14] ምክርና መልካም ጥበብ የእኔ ነው፤ ማስተዋል እኔ ነኝ፥ ብርታትም አለኝ። [15] ነገሥታት
በእኔ ይነግሣሉ፥ ሹማምቶችም የቀናውን ነገር ይደነግጋሉ። [16] አለቆች በእኔ ያዝዛሉ፥ ከቡራንና የምድር
ፈራጆችም ሁሉ። [17] እኔ የሚወድዱኝን እወድዳለሁ፥ ተግተው የሚሹኝም ያገኙኛል። [18] ብልጥግናና
ክብር በእኔ ዘንድ ነው፥ ብዙ ሀብትና ጽድቅም። [19] ፍሬዬም ከምዝምዝ ወርቅ ይሻላል፥ ቡቃያዬም
ከተመረጠች ብር። [20] እኔ በጽድቅ መንገድ እሄዳለሁ፥ በፍርድም ጎዳና መካከል፥ [21] ለሚወድዱኝ ርስት
አወርሳቸው ዘንድ ቤተ መዛግብታቸውንም እሞላ ዘንድ። [22] እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ
አደረገኝ፥ በቀድሞ ሥራው መጀመሪያ። [23] ከጥንቱ ከዘላለም ጀምሮ ተሾምሁ፤ ምድር ከመፈጠርዋ
አስቀድሞ። [24] ቀላያት ገና ሳይኖሩ እኔ ተወለድሁ፥ የውኃ ምንጮች ገና ሳይፈልቁ። [25] ተራሮች ገና

ሳይመሠረቱ፥ ከኮረብቶች በፊት እኔ ተወለድሁ፥ 26 ምድሪቱንና ሜዳውን ገና ሳይፈጥር፤ የመጀመሪያውን
የዓለም አፈር። 27 ሰማዮችን በዘረጋ ጊዜ አብሬ ነበርሁ፥ በቀላያት ፊት ክበብን በደነገገ ጊዜ፥ 28 ደመናትን
በላይ ባዘጋጀ ጊዜ፥ የቀላይን ምንጮች ባጸና ጊዜ፥ 29 ለባሕርም ዳርቻን በወሰነ ጊዜ ውኃ ከትእዛዙ
እንዳያልፍ፥ የምድርን መሠረት በመሠረተ ጊዜ፥ 30 የዚያን ጊዜ እኔ በእርሱ ዘንድ ዋና ሠራተኛ ነበርሁ፤
ዕለት ዕለት ደስ አሰኘው ነበርሁ፥ በፊቱም ሁልጊዜ ደስ ይለኝ ነበርሁ፥ 31 ደስታዬም በምድሩ ተድላዬም
በሰው ልጆች ነበረ። 32 አሁንም ልጆቼ ሆይ፥ ስሙኝ፤ መንገዴንም የሚጠብቁ ምስጉኖች ናቸው። 33
ትምህርቴን ስሙ፥ ጠቢባንም ሁኑ፥ ቸል አትበሉትም። 34 የሚሰማኝ ሰው ምስጉን ነው ዕለት ዕለት
በቤቴ መግቢያ የሚተጋ፥ የደጄንም መድረክ የሚጠብቅ። 35 እኔን ያገኘ ሕይወትን ያገኛልና።
ከእግዚአብሔርም ሞገስን ያገኛልና። 36 እኔን ያጣ ግን ራሱን ይጐዳል፤ የሚጠሉኝ ሁሉ ሞትን
ይወድዳሉ።

## ምዕራፍ 9

1 ጥበብ ቤትዋን ሠራች፥ ሰባቱንም ምሰሶችዋን አቆመች። 2 ፍሪዳዋን አረደች፥ የወይን ጠጅዋን
ደባለቀች፥ ማዕድዋን አዘጋጀች። 3 ባሪያዎችዋን ልካ በከተማይቱ ከፍተኛ ስፍራ ላይ ጠራች። 4 አላዋቂ
የሆነ ወደዚህ ፈቀቅ ይበል፤ አእምሮ የጐደላቸውንም እንዲህ አለች። 5 ኑ፥ እንጀራዬን ብሉ፥
የደባለቅሁትንም የወይን ጠጅ ጠጡ። 6 አላዋቂነትን ትታችሁ በሕይወት ኑሩ፥ በማስተዋልም መንገድ
ሂዱ። 7 ፌዘኛን የሚገሥጽ ለራሱ ስድብን ይቀበላል፥ ኀጥአንም የሚዘልፍ ነውርን ያገኛል። 8 ፌዘኛን
አትገሥጽ እንዳይጠላህ፤ ጠቢብን ገሥጽ ይወድድህማል። 9 ለጠቢብ ሰው ትምህርትን ስጠው፥
ጥበብንም ያበዛል፤ ጽድቅንም አስተምረው፥ እውቀትንም ያበዛል። 10 የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን
መፍራት ነው፤ ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው። 11 ዘመንህ በእኔ ይበዛልና፥ የሕይወትህም ዕድሜ
ይጨመርልሃልና። 12 ጠቢብ ብትሆን ለራስህ ጠቢብ ትሆናለህ፥ ፌዘኛም ብትሆን ፌዘኛነትህን ለብቻህ
ትሸከማለህ። ፍን የሚቀጥለው ከግሪክ የተጨመረ ነው። ልጅ ለራስህ አዋቂ ብትሆን ለባልንጀራህም
አዋቂ ትሆናለህ፤ ለራስህ ክፉ ብትሆን ግን ክፋትህን ትማራለህ። ሐሰትን የሚያዘጋጅ ሰው ነፋሳትን
እንደሚያዘጋጅ ሰው ነው፤ የሚበርር ወፍንም እንደሚከተል ይመስላል። የወይኑ ቦታ መንገዱን ተው፤
የሚሠማራባትን መንገድ ዘነጋ፤ ወደ ምድረ በዳ ይሄዳል ለጥም ወደ ተሠራች አገር ይሄዳል፤ የማያፈራ
የማይጠቅም ገንዘብንም በእጁ ይሰበስባል።

13 ሰነፍ ሴት ሁከተኛ ናት፤ አሳብ የላትም፥ አንዳችም አታውቅም። 14 በቤትዋ ደጅ በከተማይቱ ከፍተኛ
ስፍራ በወንበር ላይ ትቀመጣለች፥ 15 በመንገድ የሚያልፉትን አካሄዳቸውንም ያቀኑትን ለመጥራት። 16
አላዋቂ የሆነ ወደዚህ ፈቀቅ ይበል፤ አእምሮ የጐደለውንም እንዲህ አለች። 17 የስርቆት ውኃ ይጣፍጣል፥
የተሸሸገም እንጀራ ደስ ያሰኛል። 18 ነገር ግን እርሱ ሙታን ከዚያ እንዳሉ፥ እድምተኞችዋም በሲኦል
ጥልቀት እንዳሉ አያውቅም።

## ምዕራፍ 10

1 የሰሎሞን ምሳሌዎች። ጠቢብ ልጅ አባቱን ደስ ያሰኛል፤ ሰነፍ ልጅ ግን ለእናቱ ኀዘን ነው። 2

አታደርግም። 13 የበግ ጠጕርና የተልባ እግር ትፈልጋለች፥ በእጆችዋም ደስ ብሎአት ትሠራለች። 14
እርስዋ እንደ ነጋዴ መርከብ ናት፤ ከሩቅ አገር ምግብዋን ትሰበስባለች። 15 ገና ሌሊት ሳለ ትነሣለች
ለቤትዋም ሰዎች ምግባቸውን፥ ለገረዶችዋም ተግባራቸውን ትሰጣለች። 16 እርሻንም ተመልክታ
ትገዛለች፤ ከእጅዋም ፍሬ ወይን ትተክላለች። 17 ወገብዋን በኃይል ትታጠቃለች፥ ክንድዋንም
ታበረታለች። 18 ንግድዋ መልካም እንደ ሆነ ትመለከታለች፤ መብራትዋ በሌሊት አይጠፋም። 19 እጅዋን
ወደ አመልማሎ ትዘረጋለች፥ ጣቶችዋም እንዝርትን ይይዛሉ። 20 እጅዋን ወደ ድሀ ትዘረጋለች፥ ወደ
ችግረኛም እጅዋን ትሰድዳለች። 21 ለቤትዋ ሰዎች ከበረዶ ብርድ የተነሣ አትፈራም፥ የቤትዋ ሰዎች ሁሉ
እጥፍ ድርብ የለበሱ ናቸውና። 22 ለራስዋም ግብረ መርፌ ስጋጃ ትሠራለች ጥሩ በፍታና ቀይ ግምጃ
ትለብሳለች። 23 ባልዋ በአገር ሽማግሌዎች መካከል በሸንጎ በተቀመጠ ጊዜ በበር የታወቀ ይሆናል። 24
የበፍታ ቀሚስ እየሠራች ትሸጣለች፥ ለነጋዴም ድግ ትሸጣለች። 25 ብርታትና ከበሬታ ልብስዋ ነው፤
በኋላም ዘመን ላይ ትስቃለች። 26 አፍዋን በጥበብ ትከፍታለች፤ የርኅራኄም ሕግ በምላስዋ አለ። 27
የቤትዋንም ሰዎች አካሄድ በደኅና ትመለከታለች፥ የሀኬትንም እንጀራ አትበላም። 28 ልጆችዋ ይነሣሉ፥
ምስጋናዋንም ይናገራሉ፤ ባልዋ ደግሞ እንዲህ ብሎ ያመሰግናታል። 29 መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ፥
አንቺ ግን ከሁሉ ትበልጫለሽ። 30 ውበት ሐሰት ነው፥ ደም ግባትም ከንቱ ነው፤ እግዚአብሔርን
የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች። 31 ከእጅዋ ፍሬ ስጡአት፥ ሥራዎችዋም በሸንጎ ያመስግኑአት።

# መጽሐፈ መክብብ

## ምዕራፍ 1

1 በኢየሩሳሌም የነገሠ የሰባኪው የዳዊት ልጅ ቃል። 2 ሰባኪው። ከንቱ፥ ከንቱ፥ የከንቱ ከንቱ ሁሉ ከንቱ
ነው ይላል። 3 ከፀሐይ በታች በሚደክምበት ድካም ሁሉ የሰው ትርፉ ምንድር ነው 4 ትውልድ ይሄዳል፥
ትውልድም ይመጣል፤ ምድር ግን ለዘላለም ነው። 5 ፀሐይ ትወጣለች፥ ፀሐይም ትገባለች፥
ወደምትወጣበትም ስፍራ ትቸኵላለች። 6 ነፋስ ወደ ደቡብ ይሄዳል፥ ወደ ሰሜንም ይዞራል፤ ዘወትር
በዙረቱ ይዞራል፥ ነፋስም በዙረቱ ደግሞ ይመለሳል። 7 ፈሳሾች ሁሉ ወደ ባሕር ይሄዳሉ፥ ባሕሩ ግን
አይሞላም፤ ፈሳሾች ወደሚሄዱበት ስፍራ እንደ ገና ወደዚያ ይመለሳሉ። 8 ነገር ሁሉ ያደክማል ሰው
ይናገረው ዘንድ አይችልም፤ ዓይን ከማየት አይጠግብም፥ ጆሮም ከመስማት አይሞላም። 9 የሆነው ነገር
እርሱ የሚሆን ነው፥ የተደረገውም ነገር እርሱ የሚደረግ ነው፤ ከፀሐይም በታች አዲስ ነገር የለም። 10
ማንም። እነሆ፥ ይህ ነገር አዲስ ነው ይል ዘንድ ይችላልን እርሱ ከእኛ በፊት በነበሩት ዘመናት
ተደርጎአል። 11 ለፊተኞቹ ነገሮች መታሰቢያ የላቸውም፤ ከኋለኞቹም ነገሮች ከእነርሱ በኋላ በሚነሡት
ሰዎች ዘንድ መታሰቢያ አይገኝላቸውም።

12 እኔ ሰባኪው በእስራኤል ላይ በኢየሩሳሌም ንጉሥ ነበርሁ። 13 ከሰማይም በታች የተደረገውን ሁሉ
በጥበብ እፈልግና እመረምር ዘንድ ልቤን አተጋሁ፤ እግዚአብሔር ይደክሙባት ዘንድ ይህችን ለሰው
ልጆች የሰጠ ክፉ ጥረት ናት። 14 ከፀሐይ በታች የተሠራውን ሥራ ሁሉ አየሁ፤ እነሆም፥ ሁሉ ከንቱ
ነው፥ ነፋስንም እንደ መከተል ነው። 15 ጠማማ ይቀና ዘንድ አይችልም፤ ጐደሎም ይቈጠር ዘንድ
አይችልም። 16 እኔ በልቤ። እነሆ፥ ከእኔ አስቀድመው በኢየሩሳሌም ላይ ከነበሩት ሁሉ ይልቅ ጥበብን
አብዝቼ ጨመርሁ፤ ልቤም ብዙ ጥበብንና እውቀትን ተመለከተ ብዬ ተናገርሁ። 17 ጥበብንና ዕብደትን
ሞኝነትንም አውቅ ዘንድ ልቤን ሰጠሁ፤ ይህም ደግሞ ነፋስን እንደ መከተል እንደ ሆነ አስተዋልሁ። 18
በጥበብ ሙብዛት ትካዜ ይበዛልና፤ እውቀትንም የሚጨምር ኀዘንን ይጨምራልና።

## ምዕራፍ 2

1 እኔ በልቤ። ና በደስታም እፈትንሃለሁ፥ መልካምንም ቅመስ አልሁ፤ ይህም ደግሞ እነሆ ከንቱ ነበረ። 2
ሳቅን። ዕብድ ነህ፤ ደስታንም። ምን ታደርጋለህ አልሁት። 3 የሰው ልጆች በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ
ከፀሐይ በታች ሊሠሩት መልካም ነገር ምን እንደ ሆነ እስካይ ድረስ ልቤ በጥበብ እየመራኝ፥ ሰውነቴን
በወይን ጠጅ ደስ ለማሰኘት ስንፍናንም ለመያዝ በልቤ መረመርሁ። 4 ትልቅ ሥራን ሠራሁ፥ ቤቶችንም
አደረግሁ፥ ወይንም ተከልሁ፤ 5 አትክልትንና ገነትን አደረግሁ፥ ልዩ ልዩ ፍሬ ያለባቸውንም ዛፎች
ተከልሁባቸው፤ 6 በዱር የተተከሉትን ዛፎች አጠጣበት ዘንድ የውኃ ማጠራቀሚያ አደረግሁ። 7
ወንዶችንና ሴቶችን ባሪያዎች ገዛሁ፥ የቤት ውልድ ባሪያዎችም ነበሩኝ፤ ከእኔ አስቀድመው በኢየሩሳሌም
ከነበሩት ሁሉ ይልቅ ብዙ ከብቶችና መንጋዎች ነበሩኝ። 8 ብርንና ወርቅን የከበረውንም የነገሥታትና

